በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ETHIOPIAN CUSTOMS AUTHORITHY
የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
ADDIS ABABA KALITY CUSTOMS BRANCH OFFICE
የውስጥ ማስታወሻ /INTER OFFICE MEMO/

ቁጥር፡ ስ/አ/ጽ/ቤት 15/2011

ቀን፡ መስከረም 28 ቀን 2011 ዓ.ም

- ለ፡- መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች በመንግስት ለተሠጡ መ/ማ/ቡድን
- ለ፡- መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ክሊራስ ዩኒት

❖ ከ፡- ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
ኢ.አ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

አዝዘው ጫኔ አበበ
ስራ አስኪያጅ
Azizew Chanie Abebe
Manager

ጉዳዩ፡- ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት እንዲሰጡ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገቡ ተሽከርካሪዎችን ይመለከታል፣

አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 41/2007 መሠረት አገልግሎት እየተሠጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ሆኖም የጤና ጥበቃ ሚ/ር የህክምና ቦርድ ማስረጃ እንዲሰጡ ወክለና የተሰጣቸው አንዳንድ ሆስፒታሎች ለመብቱ ተጠቃሚዎች የሚሠጧቸዉ የህክምና ማስረጃዎች ግልፅነት የጎደላቸዉ ሆኖ ስለተገኘ በሀኪሞች ቦርድ የሚሰጡ ማስረጃዎች ሊያሟሉ የሚገቡ መረጃዎች ተጠቅሰው ከአምራችና ወጪ ንግድ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት በቁጥር 4.2/209/11 በቀን 23/01/2011 ዓ.ም ተገልፆልናል፡፡

በዚሁ መሠረት ለአካል ጉዳተኞች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ለሚገቡ ዕቃዎች ከሀኪሞች ቦርድ የሚፃፉው የህክምና ማረጋገጫ ከላይ ቀንና ቋሚ ጉዳት በተጠቀሰው ደብዳቤ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን ያሟሉ ሆነው ሲገኙ ብቻ አገልግሎቱ እንዲሰጥ አሳስባለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፡-

❖ ለ፡- ጉምሩክ ጉዳዮች ም/ሥራ አስኪያጅ
❖ ለ፡- ህግ ማስከበር ም/ሥራ አስኪያጅ
❖ ለ፡- ገላን ተርሚናል ጉምሩክ ማስተባበሪያ
❖ ለ፡- ጉ/ሥ/ሥ/አ/ስ/ሂደት
❖ ለ፡- ድንገተኛ ፍተሻ ቡድን
❖ ለ፡- ኢንተለጀንስ ቡድን
ኢ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር / Ref. No ሒ-ጊ/2009/11
ቀን / Date 23 መስከረም 2011

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች
<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት እንዲሰጡ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገቡ ተሽከርካሪዎችን ይመለከታል</u>

የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር በቀን 16/01/2011 በቁጥር ሐ5/ከ/1/10 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር በጻፈውና ለባለሥልጣኑ ግልባጭ ባደረገው ደብዳቤ መንግስት የአካል ጉዳተኞችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማሳደግ እንዲቻል አካል ጉዳተኛ የሆነ ሰው ለግል አገልግሎት የሚያውለው ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲያስገባ መመሪያ ቁጥር 41/2007 አውጥቶ ከሐምሌ 1/2007 ዓም ጀምሮ ሥራ ላይ ማዋሉን ጠቅሶ ይሁንና በመመሪያው አፈጻጸም ሚና ያላቸው ባለድረሻ አካላት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት መመሪያው ሳይሸራርፉ እንዲፈፅም በጎ ሚና እየተጫወቱ አለመሆኑን ገልጿል፡፡ ከእነዚህ መካከል የጤና ጥበቃ ሚ/ር በተለያዩ ጊዜያት የማሳሰቢያ ደብዳቤዎች የተፃፉለት ቢሆንም ምላሽ እንዳልሰጠ ገልጿል፡፡

የጤና ጥበቃ ሚ/ር የህክምና ቦርድ ማስረጃ እንዲሰጡ ውክልና የሰጣቸው አንዳንድ ሆስፒታሎች ለመብቱ ተጠቃሚዎች የሚሰጧቸው የህክምና ማስረጃዎች የመመሪያውን መንፈስ ተከትለው በግልፅና ማንም ሊረዳው በሚችለው ቋንቋ እየተፃፉ ባለመሆኑ እና የመብቱ ተጠቃሚ መሆን ለማይገባቸው ሰዎችም የህክምና ማስረጃዎች በዘፈቀደ እየተሰጡ በመሆናቸው ምክንያት መ/ቤቱ የማስረጃዎችን ትክክለኛነት አጣርቶና መርምሮ ወደ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የድጋፍ ደብዳቤ በመፃፍ ያማስተላለፉን ሥራ አስቸጋሪና ውስብስብ እንዳደረገበት ገልጧል፡፡

ይህም የሆነበት ምክንያት በመመሪያው ክፍል 1 ትርጓሜ በሚለው ሥር በተራ ቁጥር 1 "አካል ጉዳተኞች"፣ በተራ ቁጥር 7 "የመንቀሳቀስ ችግር ያለበት" እና በአንቀጽ 5 ተራ ቁጥር 2 ላይ የተገለፀውን መሠረት በማድረግ በመመሪያው በተመላከተው መሠረት የመብቱ ተጠቃሚ የሆነ አካል ጉዳተኛ የእንቅስቀሴ ችግሩን ለማቃለል ሲባል መኪና ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስገባት እንደሚፈቀድለት ግንዛቤ ተይዞ በየሆስፒታሉ በሐኪሞች ቦርድ ሊሰጡ የሚገባቸው ማስረጃዎች፡-

1. የመብቱ ተጠቃሚ የሆነ ሰው የአካል ጉዳት አይነት በማያሻማና ግልጽ በሆነ ሁኔታ በዝርዝር፣
2. የመብቱ ተጠቃሚ የሆነ ሰው በጉዳቱ ምክንያት ምንም ዓይነት የእንቅስቃሴ ድጋፍ/ የሌላ መሣሪያ/ የሌላ ሰው ድጋፍ ሳይደረግለት ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ የማይችል መሆኑን በግልጽ በማስፈር፣

3. የመብቱ ተጠቃሚ የሆነ አካል ጉዳተኛ ዘላቂ የአካል ጉዳት የደረሰበት መሆኑን በመግለጽ፣
4. የመብቱ ተጠቃሚ የሆነ አካል ጉዳተኛ በደረሰበት የአካል ጉዳት ምክንያት መኪና ለማሽከርከር መቻሉ ወይንም አለመቻሉን፣ በአማርኛ ቋንቋ ተገልጾ ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከአባሪ ደብዳቤ ጋር መላክ እንደነበረበት አስምሯል። ነገር ግን ይህ እየተደረገ ባለመሆኑ ሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊነቱን ለመወጣት መቸገሩንም አመልክቷል።

እንደ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከላይ የተገለጹ ችግሮች በየዕለቱ እያጋጠሙን ያሉ ችግሮች መሆናቸው ይታወቃል። በዚሁ ምክንያት በመመሪያ 41/2007 ክፍል ሶስት አንቀጽ 7 ላይ የተሰጡንን ኃላፊነቶች በአግባቡ እየተወጣን አይደለንም። ይህ ብቻ ሳይሆን እንደ ባለሥልጣን የአካል ጉዳተኞች በመንቀሳቀስ ችግር ብቻ ከማህበረሰባዊ፣ ከፖለቲካዊና ከኢኮኖሚያዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዳይገደቡ የተፈቀደ መብት የማይመለከታቸው ግለሰቦች እየተጠቀሙበት እያየን እንዳላየን ዝም ማለት እንደ ባለሥልጣንም ከተጠያቂነት የሚያድነን ባለመሆኑ የእርምት እርምጃ መውሰድ ተገቢ መሆኑ ላይ ታምኖበታል። ስለሆነም ከላይ ሚ/ር መ/ቤቱ የዘረዘራቸው ነጥቦች ያልተሟሉበት የጤና ምርመራ ማስረጃ ህጋዊ ነው ተብሎ ስለማይወሰድ አገልግሎት መስጠት አይቻልም።

በመሆኑም ከላይ የተዘረዘሩ ነጥቦችን በግልጽ ቋንቋ ያላካተቱ የህክምና ማስረጃዎች በተለይም "የመንቀሳቀስ ችግር ያለበት" የሚለው የመመሪያውን ትርጉም የሚያሟላ ሆኖ በአካል የቀረበው ግለሰብ መንቀሳቀስ የማይችል መሆኑን ወይንም እየተንቀሳቀሰ ያለው በሰው ሰራሽ መሣሪያ ወይንም በሰው ድጋፍ መሆኑን በግልጽ የማያመለክቱ የጤና ምርመራ ማስረጃዎች ተቀባይነት የሌላቸው በመሆኑ ከዚህ በፊት መስፈርቱን ሳያሟሉ የተስተናገዱ ተሽከርካሪዎች ላይ ህግ በሚፈቅደው መሠረት የሚወሰድ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ መስፈርቱን ለማያሟሉ ግለሰቦች ተመሳሳይ አገልግሎት እንዳይሰጥ እናሳስባለን።

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርም ይህንኑ የማያሟሉ የጤና ተቋማት የሚሰጡትን ማስረጃዎች ውድቅ እንዲያደርግ አስተያየት እያቀረብን ከዚህ የተለየ አቅጣጫ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር እስከሚሰጠን ድረስ መንቀሳቀስ የማይችል የሚለውን ሀረግ ትርጓሜ የማያሟሉ ማስረጃዎችን የማንቀበል መሆናችንን እንዲያውቅ የዚህ ደብዳቤ ግልባጭ ተመዝግቧል።

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ
- ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር
- ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር
- ለጤና ጥበቃ ሚ/ር

  አዲስ አበባ
- ለጉምሩክ ዘርፍ
- ለህግ ማስከበር ዘርፍ
- ለኢንተለጀንስ ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

  ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
MINISTRY OF LABOUR AND SOCIAL AFFAIRS

ቁጥር No. ...
ቀን 17 6 መስከረም 2011
Date

ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>

**ጉዳዩ፡- <u>ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት እንዲሰጡ ከቀረጥና ታክስ ነጻ የሚገቡ ተሽከርካሪዎችን ይመለከታል፣</u>**

መንግሥት የአካል ጉዳተኞችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማሳደግ እንዲቻል አካል ጉዳተኛ የሆነ ሰው ለግል አገልግሎት የሚያውለው ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲያስገባ መመሪያ ቁጥር 41/2007ን አውጥቶ ከሐምሌ 1/2007 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ ማዋሉ ይታወቃል። መመሪያውን ተፈፃሚ ለማድረግ የብዙ ባለድርሻ አካላትን ትብብርና ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ አስፈፃሚ ተቋማት በጋራና በግል ምን ማከናወን እንዳለባቸው በመመሪያው ላይ በግልፅ ተመላክቷል።

የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት መመሪያውን ሳይሸራርፉ እንዲፈፀሙ መስሪያ ቤታችን በተለያዩ ጊዜያት የማሳሰቢያ ደብዳቤዎችን የጻፈ ቢሆንም በተለይ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የህክምና ቦርድ ማስረጃ እንዲሰጡ ውክልና በተሰጣቸው (ቅዱስ ጳውሎስ ሚሌኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፣ ዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል፣ ጥቁር አንበሳ አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ ሀዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል እና አይደር ሪፈራል ሆስፒታል) አንዳንድ ሆስፒታሎች ለመብቱ ተጠቃሚዎች የሚሰጧቸው የህክምና ማስረጃዎች የመመሪያውን መንፈስ ተከትለው በግልፅና ማንም ሊረዳው በሚችለው ቋንቋ እየተፃፉ ባለመሆኑ እና የመብቱ ተጠቃሚ መሆን ለማይገባቸው ሰዎችም የህክምና ማስረጃዎች በዘፈቀደ እየተሰጡ በመሆናቸው ምክንያት መስሪያ ቤታችን የማስረጃዎችን ትክክለኛነት አጣርቶና መርምሮ ወደ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የድጋፍ ደብዳቤ በመፃፍ የማስተሳሰሩን ሥራ አስቸጋሪና ውስብስብ አድርጎበታል።

የፖ.ሣ.ቁ. 2056 ስልክ ፋክስ(251-11)551 8379.501220
P.O.Box 2056 Tel (+251-11)551 7080/515249 Fax (+251-11)551 1316
Web site: www.molsa.gov.et
ኢ-ሜይል E-mail molsa.comp@ethionet.et
እባክዎን መልስ ሲጽፉ የደብዳቤያችንን ቁጥር እንዲጠቅሱ ይጠየቃሉ/Please Quote Our Reference Number

ይህም የሆነበት ምክንያት በመመሪያው ክፍል 1 ትርጓሜ በሚለው ሥር በተራ ቁጥር 1 "አካል ጉዳተኞች"፣ በተራ ቁጥር 7 "የመንቀሳቀስ ችግር ያለበት" እና በአንቀጽ 5 ተራ ቁጥር 2 ላይ የተገለፀውን መሠረት በማድረግ በመመሪያው በተመላከተው መሠረት የመብቱ ተጠቃሚ የሆነ አካል ጉዳተኛ የእንቅስቃሴ ችግሩን ለማቃለል ሲባል መኪና ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስገባት እንደሚፈቀድለት ግንዛቤ ተይዞ በየሆስፒታሉ በሐኪሞች ቦርድ ሊሰጡ የሚገባቸው ማስረጃዎች፡-

1/ የመብቱ ተጠቃሚ የሆነ ሰው የአካል ጉዳት አይነት በማያሻማና ግልጽ በሆነ ሁኔታ በዝርዝር፣

2/ የመብቱ ተጠቃሚ የሆነ ሰው በጉዳቱ ምክንያት ምንም ዓይነት የእንቅስቃሴ ድጋፍ/ የሌላ መሣሪያ/ የሌላ ሰው ድጋፍ ሳይደረግለት ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ የማይችል መሆኑን በግልጽ በማስፈር፣

3/ የመብቱ ተጠቃሚ የሆነ አካል ጉዳተኛ ዘላቂ የአካል ጉዳት የደረሰበት መሆኑን በመግለጽ፣

4/ የመብቱ ተጠቃሚ የሆነ አካል ጉዳተኛ በደረሰበት የአካል ጉዳት ምክንያት መኪና ለማሽከርከር መቻሉ ወይንም አለመቻሉን፣ በአማርኛ ቋንቋ ተገልፆ ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከአባሪ ደብዳቤ ጋር መላክ ነበረበት። ሆኖም ይህ በአግባቡ ተፈፃሚ እየሆነ አይደለም።

በተጨማሪም በመመሪያው ክፍል ሶስት ቁጥር ዘጠኝ የክልልና የከተማ ትራንስፖርት ቢሮዎች በሚለው ስር ፡-

1. ከቀረጥ ነፃ እንዲሆን የተፈቀደውን ተሽከርካሪ ለመለየት የሚያስችል በተሽከርካሪው አካል ላይ በሚታይ ቦታ የአካል ጉዳተኞችን ምቹ ሁኔታ የሚገልጽ ዓለም አቀፍ ልዩ ስሌዳ ወይም ሊለወጥ የማይችል ልዩ ምልክት ያደርጋል።

2. የሚመለከተው የትራንስፖርት ቢሮ በዚህ መመሪያ መሠረት ከቀረጥና ታክስ ነፃ የገቡ ተሽከርካሪዎች ለዓመታዊ ዕድሳት ሲቀርቡ ከሠራተኛ እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የድጋፍ ደብዳቤ እንዲያቀርቡ ያደርጋል። የሚቀርቡትንም የድጋፍ ደብዳቤዎች ዋና ቅጂ በፋክስ መልዕክት እንዲረጋገጡ ያደርጋል።

[illegible]

3 የሚመለከተው [illegible] ዘዴ [illegible] ለዓመታዊ ለድሳት የቀረቡ የመብት ተጠቃሚዎችን እና የተሽከርካሪዎቻቸውን ዝርዝር የዓመታዊ ለድሳት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስትሩ እና ለባለሥልጣኑ ይልካል ይላል ፡፡ ይሁን እንጂ እንዚህ ተግባራት ተፈጻሚ እየተደረጉ አይደለም፡፡

ስለሆነም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር መመሪያው በአግባቡ ተፈጻሚ እንዲሆን በተለይ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የክልልና የከተማ ትራንስፖርት ቢሮዎች እንዲሁም ለሌሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ባድርሻ አካላት መመሪያውን መሰረት በማድረግ የተሰጣቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ጥብቅ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርግ እንዲሁም በስራ ላይ ያለውን መመሪያ በመፈተሽ የመመሪያውን ተፈጻሚነት የሚያሳድግና ለአሰራር የሚያመች በየጊዜው የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲቋቋም እየጠየቅን ሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ከአሁን በፊት በተለያዩ ጊዜያት ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት መመሪያውን በአግባቡ መፈጸም እንደሚገባቸው ያሳሰብንባቸውን ደብዳቤዎች 10 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ ልከናል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፦
- ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
- ለፌደራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
- ለፌ ራል ትራ ስፖርት ባለስልጣን

አዲስ አበባ

እንዲያውቁት፣
- ለ ቡር የማኅበራዊ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ

ሠ.ማ.ጉ.ሚ/ር

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር / Ref. No 4-0/92/10

ቀን / Date 28 ነሐሴ 2010

ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
<u>አዲስ አበባ</u>

መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች፣ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ በጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ከጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነጻ ስለሚያስገቧቸው ዕቃዎች በመጣው መመሪያ ቁጥር 79/2005 በተሰጠው ትርጉም መሰረት ሚኒ ባስ ማለት ታጣፊ ወንበሮችን ሳይጨምር ከ10 ያላነሰ እና ከ12 ያልበለጠ መቀመጫ ያለው የሰው መጓጓዣ ተሽከርካሪ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ሆኖም የመብቱ ተጠቃሚዎች እስከ 15 ሰው መጫን የሚችል ሚኒ ባስ እያስመጡ በመሆኑ በአሰራር ላይ ችግር አስከትሏል፡፡

በሌላ በኩል የምንጠቀምበት የተጣጣመ የሸቀጦች አመዳደብ ስርዓት ሚኒ ባስ የሚለውን ቃል ባይጠቀምም ተሽከርካሪዎችን በሚጭኑት የሰው ቁጥር መሰረት በተለያዩ የታሪፍ ቁጥሮች ላይ ይመድባቸዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ለሰው ማጓጓዣነት የሚያገለግሉ ተሽከርካሪዎች በታሪፍ አንቀጽ 87.02 ሥር የሚመደቡ ናቸው፡፡ ሾፌሩን ጨምሮ ከአስር (10) እስከ አስራ አምስት (15) ሰው መጫን የሚችሉ ተሽከርካሪዎች እንደ በሞተር ዓይነት ተለይተው ባለዲዝል ሞተሮች በታሪፍ ቁጥር 8702.1010 ቤንዚን ወይም ሌላ ነዳጅ የሚጠቀሙ ሞተሮች ያላቸው ደግሞ በታሪፍ ቁጥር 8702.9010 ላይ ተመድበው በሁለቱም ታሪፍ ቁጥሮች ላይ የሚመደቡት ተሽከርካሪዎች እኩል 35 በመቶ የጉምሩክ ቀረጥ የተጣለባቸው ናቸው፡፡

ተሽከርካሪዎች የሚጭኑት የሰው ቁጥር 12 ሆነ 15 እንደሞተር ዓይነታቸው በአንድ ታሪፍ ቁጥር ላይ የሚመደቡ ናቸው፡፡ የሚጭኑት የሰው ቁጥር 12 ወይም 15 መሆኑ ለውጥ አያመጣም፡፡ የታሪፍ አወቃቀሩንም ስናይ ተሽከርካሪዎች የሚጭኑት የሰው ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ ከኤክሳይዝ ታክስ ነጻ እየሆኑ እና የጉምሩክ ቀረጣቸው እየቀነሰ ይመጣል፡፡ ይህም ተሽርካሪዎች የሚጭኑት የሰው ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ የበለጠ ለህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት እንደሚውሉ ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት መበረታታት ያለበት 12 ሰው መጫን ከሚችለው ይልቅ 15 ሰው መጫን የሚችለው ተሽከርካሪ ነው፡፡

በመሆኑም ጉዳዮ የመጨረሻ እልባት እስኪሰጠው ድረስ ሚኒባስን በተመለከተ በእንጥልጥል ላይ ያሉ ጉዳዮች 15 (አስራ አምስት) ሰው መጫን የሚችል ተብሎ የተስተካከለ መሆኑን እየገለጽን በዚሁ አግባብ እንዲፈጸሙ የተወሰነ መሆኑን እናሳውቃለን።

ከሠላምታ ጋር

ተስፋዬ ቱሉ መልካ
የጉምሩክ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ
- ለጉምሩክ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
  ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

በመሆኑም ጉዳዮ የመጨረሻ እልባት እስኪሰጠው ድረስ ሚኒባስን በተመለከተ በእንጥልጥል ላይ ያሉ ጉዳዮች 15 (አስራ አምስት) ሰው መጫን የሚችል ተብሎ የተስተካከለ መሆኑን እየገለጽን በዚሁ አግባብ እንዲፈጸሙ የተወሰነ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ተስፋዬ ቱሉ መልካ
የጉምሩክ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ</u>
- ለጉምሩክ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
<u>ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር Ref. No 4/0/92/10
ቀን Date 28 ነሐሴ 2010

ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
<u>አዲስ አበባ</u>

መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች፣ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ በጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ከጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነጻ ስለሚያስገቧቸው ዕቃዎች በመጣው መመሪያ ቁጥር 79/2005 በተሰጠው ትርጉም መሰረት ሚኒ ባስ ማለት ታጣፊ ወንበሮችን ሳይጨምር ከ10 ያላነሰ እና ከ12 ያልበለጠ መቀመጫ ያለው የሰው መጓጓዣ ተሽከርካሪ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ሆኖም የመብቱ ተጠቃሚዎች እስከ 15 ሰው መጫን የሚችል ሚኒ ባስ እያስመጡ በመሆኑ በአሰራር ላይ ችግር አስከትሏል፡፡

በሌላ በኩል የምንጠቀምበት የተጣጣመ የሸቀጦች አመዳደብ ስርዓት ሚኒ ባስ የሚለውን ቃል ባይጠቀምም ተሽከርካሪዎችን በሚጭኑት የሰው ቁጥር መሰረት በተለያዩ የታሪፍ ቁጥሮች ላይ ይመድባቸዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ለሰው ማጓጓዣነት የሚያገለግሉ ተሽከርካሪዎች በታሪፍ አንቀጽ 87.02 ሥር የሚመደቡ ናቸው፡፡ ሾፌሩን ጨምሮ ከአስር (10) እስከ አስራ አምስት (15) ሰው መጫን የሚችሉ ተሽከርካሪዎች እንደ በሞተር ዓይነት ተለይተው ባለዲዝል ሞተሮች በታሪፍ ቁጥር 8702.1010 ቤንዚን ወይም ሌላ ነዳጅ የሚጠቀሙ ሞተሮች ያላቸው ደግሞ በታሪፍ ቁጥር 8702.9010 ላይ ተመድበው በሁለቱም ታሪፍ ቁጥሮች ላይ የሚመደቡት ተሽከርካሪዎች እኩል 35 በመቶ የጉምሩክ ቀረጥ የተጣለባቸው ናቸው፡፡

ተሽከርካሪዎች የሚጭኑት የሰው ቁጥር 12 ሆነ 15 እንደሞተር ዓይነታቸው በአንድ ታሪፍ ቁጥር ላይ የሚመደቡ ናቸው፡፡ የሚጭኑት የሰው ቁጥር 12 ወይም 15 መሆኑ ለውጥ አያመጣም፡፡ የታሪፍ አወቃቀሩንም ስናይ ተሽከርካሪዎች የሚጭኑት የሰው ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ ከኤክሳይዝ ታክስ ነጻ እየሆኑ እና የጉምሩክ ቀረጣቸው እየቀነሰ ይመጣል፡፡ ይህም ተሽርካሪዎች የሚጭኑት የሰው ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ የበለጠ ለህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት እንደሚውሉ ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት መበረታታት ያለበት 12 ሰው መጫን ከሚችለው ይልቅ 15 ሰው መጫን የሚችለው ተሽከርካሪ ነው፡፡

ቁጥር 5.6.0/881/11
Ref. No

ቀን 04 ጥር 2011
Date

ገቢ ቁጥር 01/9.2/11
ገጽ ቁጥር 594

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ለአዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

አዳማ

ጉዳዩ፡-**የሕግአስተያየት መስጠትን ይመለከታል**

በቁጥር 8.0/34/761 በ02/13/10 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በመመሪያ ቁጥር 41/2007 አንቀጽ 2/7/ የመንቀሳቀስ ችግር ያለበት ተብሎ የተቀመጠው ትርጉምና የማስፈፀም ስልጣንና ኃላፊነቱ የማን እንደሆነና ፣እንዲሁም በደረሰበት የአካል ጉዳት ምክንያት በሰው ሰራሽ እንቅስቃሴ ድጋፍ ወይም በደረሰበት የአካል ጉዳት ምክንያት በሌላ መሳሪያ ድጋፍ ወይም በደረሰበት የአካል ጉዳት ምክንያት በሌላ ሰው ድጋፍ በስተቀር ሊንቀሳቀስ የማይችል አካል ጉዳተኛ ማለት ምን ምን እንደሚያካትት የሕግ አስተያየት መጠየቃችሁ ይታወሳል።

በዚህም መሰረት በመመሪያ ቁጥር 41/2007 አንቀጽ 6 የመብቱ ተጠቃሚዎች ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት ማሟላት ከሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ በንዑስ ቁጥር 1/ለ/ እና /ሐ/ የተዘረዘሩት ሲሆን እነዚህም በሀገር ውስጥ ከሚገኙና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እውቅና ከተሰጣቸው ሆስፒታል አካል ጉዳተኛ መሆናቸውንና የጉዳቱን አይነት የሚያረጋግጥ በሀኪሞች ቦርድ የተሰጠ የህክምና ማስረጃ ማቅረብ በተጨማሪም ከሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአካል ጉዳተኝነት ማረጋገጫ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ እንዳለባቸው ያስቀምጣል ። ስለዚህ የመንቀሳቀስ ችግር አለበት በማለት ማስረጃ የሚሰጠው ከጤና ጥበቃ ሚ/ር ዕውቅና የተሰጠው የሀኪሞች ቦርድ እና የሠራተኛና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚ/ር መሆኑን በመመሪያው ላይ በግልጽ የተቀመጠ ስለሆነ ኃላፊነቱ የእነዚህ ድርጅቶች ነው ነገር ግን በመመሪያው አንቀጽ 7/2/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የመብቱ ተጠቃሚ በቀረጥና ታክስ ነፃ ለመስተናገድ እና ተሽከርካሪውን ለመረከብ በአካል እንዲቀርብ ማስደረግ እንዳለበት በግልጽ ይደነግጋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ምንም እንኳን አካል ጉዳተኛ ነው በራሱ ሊንቀሳቀስ አይችልም ተብሎ




ስልክ ቁ / Tel. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ -ኢትዮጵያ

ከሚመለከታቸው አካላት ማስረጃ ቢሰጠውም ባለስልጣኑ ጋር ሲቀርብ በግልጽ መንቀሳቀስ የማችል መሆኑን ማረጋገጥ ፤በራሱ ያለምንም ድጋፍ መንቀሳቀስ የሚችል ከሆነ ምንም እንኳን ማስረጃውን የሰጡት አካላት ቢኖሩም ማስተናገድ የለብንም። አንዱ የመብቱ ተጠቃሚ በአካል መቅረብ አለበት የተባለው የተሰጠው ማስረጃ እና ግለሰቡ በአካል ሲቀርብ እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ጭምርም ነው። ስለዚህ በመመሪያው ላይ አንቀጽ 2/7/ የመንቀሳቀስ ችግር ያለበት ሲል በደረሰበት የአካል ጉዳት ምክንያት በሰው ሰራሽ የአካል ድጋፍ ወይም በሌላ መሣሪያ ወይም በሌላ ሰው ድጋፍ ካልሆነ በስተቀር ራሱን ችሎ መንቀሳቀስ የማይችልማለት ሆኖ ነገር ግን ራሱን ችሎ መንቀሳቀስ የሚችል ከሆነ የመብቱ ተጠቃሚ ሊሆን አይገባም በማለት አስተያየታችንን እናቀርባለን።

ከሰላምታ ጋር

Ethiopian Revenues & Customs Authority
Federal Democratic Republic of Ethiopia

[illegible] አበበ ፋሪስ
[illegible] አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር